# መመሪያ ቁጥር 238/2013

## ባንኮች ባገኙት ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ግብር የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 238/2013

ንፋስ አመጣሽ ገቢ ነው ሊባል የሚችለው ገቢ፣ በዚህ ገቢ ላይ ለክፈል የሚገባው ግብር ማጠን እና ግብሩ ሥራ ላይ የሚውልበት ቀን የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ እንደሚወሰን በገቢ ግብር አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተወሰነው የብር የምንዛሪ ተመን ለውጥ ምክንያት ባንኮች ባገኙት የሥራ እንቅስቃሴያቸው ወጤት ያልሆነ ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ግብር ማስከፈል አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትሩ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 60 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ባንኮች ባገኙት ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ግብር የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 238/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም "ባንክ" ማለት የባንክ ሥራ እንዲሠራ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም የመንግሥት ባንክ ነው፡፡

## 3. የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 11 ቀን 2017 ባደረገው የብር የምንዛሪ ለውጥ ምክንያት ባንኮች ባገኙት ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ይሆናል፡፡

## 4. የግብሩ ማስከፈያ ልክ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 11 ቀን 2017 ባደረገው የብር የምንዛሪ ለውጥ ምክንያት ማናቸውም ባንክ ባገኘው ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ 100% (መቶ በመቶ) ግብር ይከፈላል፡፡

## 5. የግብሩ ስሌት መሠረት

በዚህ መመሪያ መሠረት ለሚከፈለው ግብር ስሌት መሠረት የሚሆነው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተላከው ሪፖርት የተመለከተው እ.ኤ.አ. አክቶበር 11 ቀን 2017 በተደረገው የብር የምንዛሪ ለውጥ ምክንያት ባንኩ ያገኘው ንፋስ አመጣሽ ገቢ ማጠን ነው፡፡

## 6. የመክፈያ ጊዜ

ማናቸውም ባንክ በዚህ መመሪያ መሠረት ግብር ሊከፈልበት በሚገባ ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ግብር እስከ ታህሳስ 22 ቀን 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ወስጥ ገቢውን አስታውቆ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

## 7. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

1. በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሠረት ባንኮች ባገኙት ንፋስ አመጣሽ ገቢ ላይ ተገቢውን ግብር ይሰበስባል፡፡
2. ከንፋስ አመጣሽ ገቢ የተሰበሰበውን ግብር የሚያሳይ ሪፖርት በየወሩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

## 8. የመተባበር ግዴታ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች በብር የምንዛሪ ለውጥ ምክንያት ያገኙትን ገቢ የሚያሳይ መረጃ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በማስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 9. ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ ከ _____ ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ________ **ቀን 2010 □ም**

ዶ/ር አብርሃም ተከስተ
**የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር**